# <u>የቶማስ ጄፈርሰን መለስተኛ ደረጃትምህርት ቤት የቀለም ትምህርት ስነምግባር</u>

**<u>መግቢያናአላማ</u>**

የ IB የተማሪ ፕሮፋይል ተማሪዎች "በሀቀኝነትና በትምህርታዊ ግልጽነት፣ ጠንካራ በሆነ የፍትሃዊነት፣ የትክክለኛ ፍርድና ለግለሰብና ቡድኖችና ማህበረሰቦች ማንነት ክብርን በመስጠት መስራት" እንዳለባቸው ይገልጻል። በተጨማሪም "ለራሳቸው ድርጊቶችና ድርጊቶቻቸው ለሚያስከትሏቸው ነገሮች ሃለፊነትን መውሰድ" አለባቸው። ከጄፈርሰን IB MYPፕሮግራም አላማዎች ውስጥ አንዱ ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ ያላቸው፣ እራሳቸውን ችለው መስራት የሚችሉና በመርህ የሚመሩ ተማሪዎች እንዲሆኑ መደገፍ ነው። ይህ እንዲሆን ለማድረግ ቃላትንና ሃቦችን የሚተነትን፣ የባለድርሻ አካላትን ሚና የሚጠቅስ እና አግባብ ያልሆኑ ድርጊቶች የሚያስከትሉትን ውጤት የሚዘረዝር ትምህርት ቤት አቀፍ የትምህርታዊ ታማኝነት ፖሊሲ አዘጋጅተናል። ተማሪዎች ስለትምህርት ስኬታቸው ትክክለኛውን ምርጫ እንዲያደርጉ ደንቦቹን ማወቅ፣ መተግበር እና ጠቀሜታቸውን መረዳት አለባቸው።

**<u>ሀሳቦችናቃላት</u>**

*ማረጋገጫ*: *የአንድ ሰው ትክክለኛ ስራ ማለት የተማሪውን የግል እና ኦሪጂናል ሃሳብ ላይ የተመሰረተና ለሌሎ ሰዎች ሃሳቦችና ስራዎች ተገቢውን እውቅና የሚሰጥ ስራ ነው።*

*አእምሮአዊ ንብረት*: *የአእምሮአዊና የፈጠራ ስራ መገለጫዎች የስነ ጽሁፍ፣ የስነጥበብ ወይም ሙዚቃ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ። ሁሉም አይነቶች መከበርና በህግ መጠበቅ አለባቸው።*

*ተገቢ ያልሆኑ ባህሪያት*: *አንድ ሰው ነሌላው ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጠቃሚነት እንዲያገኝ የሚያደርግ ባህሪይ።*

**ከዚህ በታች <u>አግባብያልሆነድርጊትወይም የባህሪይ መጓደል</u> ምሳሌዎች ይገኛሉ።**

***ማጭበርበር***: *"እንደ ማጭበርበሪያ ወረቀቶች" የመሳሰሉ የማይፈቀድላቸው ነገሮችን ወደፈተና ወይም ጥያቄ ክፍል ይዞ መምጣት። ስለ ፈተና ወይም ጥያቄ መረጃዎችን ማጋራት ወይም እነዚህን መረጃዎች ያለአስተማሪው ፈቃድ መቀበል።*

***መቅዳት***: *ተማው ቢፈቅድም ባይፈቅድም የሌላ ተማሪን ስራ መውሰድና እንደራስ ስራ አድርጎ ማስገባት።*

***መኮረጅ***: *የራስ የሆነ ኦሪጂናል ስራን ማስገባት በሚጠበቅበት ወቅት በሌላ ሰው የተዘጋጀ ስራን፣ ቃላትን፣ ሃሳቦችን፣ ምስልን፣ መረጃን ወይም ማንኛውንም ሌላ ነገር መውሰድና የራስ እንደሆነ አድርጎ ማስገባት። ኩረጃ አብዛኛውን ጊዜ የሚከሰተው አንድ ሰው የሌላ ሰው ስራን ምንጫ ሳይጠቅስ ሲቀር ነው።*

***መመሳጠር***: *ሌላ ተማሪ ትምህርታዊ እምነትን እንዲያጎድል ማገዝ።*

*የኩረጃና የመመሳጠር ምሳሌዎች አብዛኛውን ጊዜ በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሚደረጉ እንዳልሆኑ ማስተዋል አስፈላጊ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ደንቦቹ ምን ማለት እንደሆኑና ተማሪዎች እንዴት በተሳካ ሁኔታ ህጎቹን ማክበር እንዳለባቸው በትክክል አለመረዳት ያጋጥማል። ተማሪዎች የትምህርታዊ ሃላፊነታቸውንና ክህሎታቸውን እያዳበሩ ሲሄዱ የትምህርት ጓደኞቻቸውን፣ ወላጆቻቸው እና መምህራን ተቀባይነት እንዳለው የመረጃ ምንጭ ማየት ይጀምራሉ።* (Carroll, J., IBMYP 2012)

***<u>አንዳንድአግባብያልሆኑተግባራትየሚከተለውንየካትታሉ</u>:***

** ፈቃድ ሳይሰጥ የሞባይል ስልክ፣ ታብሌቶችና ሌሎ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን መጠቀም*

** የማጭበርበሪያ ወረቀቶችን መጠቀም*

** የመገምገሚያ ወረቀቶችን ፈቃድ ሳይሰጥ ማግኘት*

** ያለ መምህሩ ፈቃድ የቤት ስራዎችን ለሌሎች ክፍሎች ደግሞ ማስገባት*

** እርሱ ያልሰራው ስራ ላይ የራስን ስም ጽፎ መፈረም (ማለትም የቡድን ስራ ውስጥ)*

***ተማሪዎች፣ አማካሪዎችና አስተዳዳሪዎች የትምህርታዊ አግባብ ያልሆኑ ድርጊቶችን በተመለከተ እንደየአጋጣሚው የሚለያይ ቅጣትን ይወስናሉ።***

***ሚናዎችናሃላፊነቶች***

የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለመምህራን የድጋፍ መረብ ሆነው የሚያገለግሉ ሲሆን በተጨማሪም ትምህርታዊ የእምነት ማጉደል በሚከሰትበት ወቅት አስፈላጊውን የስነምግባር እርምጃ ይወስዳሉ።

**ትምህርት ቤቱ**

- ከፖሊስነት ይልቅ የማስተማር ክህሎትን ያበረታታል
- ሁሉንም ጥፋቶች እንደ ከባድ ጥፋት ያያል (ሆን ተብለውም ሆነ በደንብ ባለመረዳት የሚከሰቱ ጥፋቶችን)

***መመህራን የትምህርታዊ ታማኝነትን በመረዳት ሂደት ወቅት እንደ ተቀዳሚ አስተማሪዎች ያገለግላሉ። ይህንን ሚናቸውን ሲወጡ:***

- ተማሪዎች የትምህርታዊ የመማር ፖሊሲዎችን መረዳታቸውን ያረጋግጣሉ
- የቤት ስራን እንዲሁም የመጨረሻ ውጤትን ለማከናወን የሚያስፈልገውን ጥረት የሚሸልሙ ጥያቄ ላይ የተመሰረቱ የግምገማ መንገዶችን መፍጠር
- ለሌሎች ሰዎች ስራ ተገቢውን እውቅና የመስጪያ መንገዶችን ማስተማር
- ቀላል፣ ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችንና የሚጠበቁ ነገሮችን ለተማሪዎች መስጠት
- ተማሪዎች የሌሎችን ስራዎች የሚጠቀሙበትን መንገድ የሚመለከት መመሪያዎችን ለተማሪዎች ለመስጠት ቋሚ (የትምህርት አካባቢ ቡድን) እቅድ ማውጣት
- ቃልኪዳኑን ማስፈረምና ትርጉሙን ማስረዳት፤ በተማሪው ቋሚ ፋይል ውስጥ እንዲቀመጥ መሰብሰብ
- በምሳሌ ማሳየት
- ተማሪዎች ራሳቸውን ችለውና በመጻነት እንዲሰሩ ማናቸውንም ለውጦች ማሳወቅ። እንዲህ አይነት ለውጦች በምሳሌዎችና መስተጋብራዊ ውይይቶች ሊነገሩ ይቻላሉ።

***ተማሪዎች***

- ሁልጊዜም የራሳቸውን ስራ ይሰራሉ
- ስራቸውን የራሳቸው እንደሆነ አድርገው ለሚያቀርቡ ለሌሎች ተማሪዎች ከማጋራት ይቆጠባሉ
- የሌሎችን የስራ ውጤት ሲጠቀሙ ተገቢውን ክትትል ያደርጋሉ እንዲሁም ሁሉንም ምስሎችና የመስመር ላይ ምንጮች ጨምሮ ለኦሪጂናል ምንጩ ወይም ጸሃፊው ተገቢውን እውቅና ይሰጣሉ
- ምጮችን መጠቀምን ለማሳየት ተገቢዎቹን መንገዶች መጠቀም - APA እና MLA የምንጭ መጥቀስ መንገዶችና ሌሎችንም ጨምሮ
- አጠራጣሪ ሁኔታ ሲኖር መምህሩን ወይም የላይብረሪ ሰራተኛውን መጠየቅ
- ፊርማቸው ከታች የሰፈረበትን ቃል ሊዳን በማክበር የትምርት ሐቀኝነታቸውን መጠበቅ

***ለምንጭ መጥቀስ እገዛዎች***

የምንጮች አይነትን፣ የምንጭ ማጣቀሻዎች ስምምነቶችንና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች በ TJMS የድር ገጽ ውስጥ IB/Academic Honesty Help በሚለው ስር ይገኛሉ

- EasyBib – ተጠቃሚዎች የተጠቀሟቸውን መጽሐፍት የሚያስቀምጥና በጥናትና በማስታወሻ መያዝ ወቅት ኩረጃን ለመከላከል የሚያግዘው የመስመር ላይ ምንጭ መጥቀሻ መሳሪያ የሆነው EasyBib ላይ የተመዘገበ አባል ነው።
- ስለ EasyBib ወይም ሌሎች የተጠቀሟቸውን መጽሐፍት የተመለከቱ ጥያቄዎች ካዎት የላይብረሪ ሰራተኛውን ያናግሩ።

**የቀለም ትምህርት ስነምግባርን ለማሻሻል ከትምህርት ቤቱ የሚጠበቁ ምን አይነት ስራዎች ናቸው?**

በሙሉ በትምህርት አመት ጊዜ ውስጥ፣ ተማሪዎች ዋና ፈተና ከመውሰዳቸው ወይም በጋራ የሰሩትን ወይም ፕሮጀክት ከማስረከባቸው በፊት ምንም አይነት የሌላ ሰው ስራ ስርቆት ላይፈጽሙ ወይም እንዳልፈጸሙ፣እንዳላሴሩ፣ ወይም ሌላ የማይገባ ነገር እንዳልሰሩ ወይም እንደማይሰሩ በቅጽ ላይ የማረጋገጫ ፊርማ ያስፍራሉ፡፡

# የቶማስ ጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
# የትምህታዊ ግልጽነት ቃል ኪዳን

እኔ፣ ______________________________________(ተማሪ) የቶማስ ጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት ግልጽነት መመሪያን አንብቤ ተረድቻለሁ። በሀቀኝነትና በትምህርታዊ ግልጽነት፣ ጠንካራ በሆነ የፍትሃዊነት፣ የትክክለኛ ፍርድና ለግለሰብና እኔ አባል ለሆንኩባቸው ቡድኖችና ማህበረሰቦች ማንነት ክብርን በመስጠት ለመስራት ቃል እገባለሁ።

ተፈርሟል: ______________________________________

(ተማሪ)

ቀን:______________________________________

እኔ, ______________________________________(ወላጅ), የቶማስ ጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት ግልጽነት መመሪያን አንብቤያለሁ።

## *ያልተገባ ስራን ብሰራ  ምን ውጤት የስከትልብኛል?*

| የጥፋት  ወይም አግባብ ያልሆነ ተግባር ደረጃ | መግለጫ | በመምህሩና በትምህርት ክፍል ሀላፊው የሚወሰዱ ተግባራት | በካውንስለሮችና በአስተዳደሮች የሚወሰዱ ተግባራት |
|---|---|---|---|
| ደረጃ  1 | **በአጋጣሚ የተደረገ** ተገቢ ያልሆነ ስራ  በልምድ ማነስ  **ለመጀመሪያ ጊዜ** ሊያገጥም ይችላል ፡፡ ተማሪዎች የራሳቸውን ያልሆንን ስራን በመጨማመር በሚያስረክቡት ስራ ሊያጋጥም ይችላል፡፡<br><br>*ለምሳሌ ሀሳቦችን በቃላት ቀምሮ ማቅረብ ወይም ትምህርታዊ ቁሶችን ያለ MLA ጥቅስ ሳያደርጉ ማቅረብን ያካትታል፡፡ የቤት ስራን ከክፍል ጓደኛ መቅዳት ወይም ለማወቅ ሳይሆን መልሱን እንዲነግሩዋቸው “እገዛ” መጠየቅ፡፡* | የመልመጃ ስራዎች፤<br>-  ስለ ወደፊት ባህሪ ለመንገርና ለመምራት ከተማሪዎች ጋር የቡድን ጉባኤ ማድረግ፣,<br>-  በቡድኑ ማስታወሻ ውስጥ የተመዘገቡ ድርጊቶች፣ ወላጅ/አሳዳጊን መገናኘት<br>-  መምህሩ ተማሪዎች የመልመጃ ስራዎችን ይፈቅዱሏቸዋል፣ ነገር ግን መልመጃውን ያሻሽሉታል፤ በዚህም ተማሪዎች አዲስ ሀሳብን ይፈጥራሉ፡፡ተማሪዎችም ሙሉ  ትምህርት ሽፋን/ጊዜ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡<br><br>ፈተና፣ ሙከራ ከሆነ፤<br>-  አንድ ተማሪ በሙከራ ወይም በፈተና መሀል ቢያታልል ወይም የሙከራው ወይም የፈተናው ውጤት ተማሪው/ዎች እንዳታለሉ የሚያስጠረጥር ከሆነ፣  መምህሩ ተማሪው/ዎች በማታለል ተሳትፈዋል ብሎ ከተጠራጠረና እንዲጠራ ከጠየቀ ነው፡፡ ይህ የማታለል ተግባር በመልመጃው በተመሳሳይ መልኩ ከተፈፀመ፣ ተማሪው/ዋ ለሙሉ የትምህርት ሽፋን/ጊዜ ሙከራ የተለየ ቅጂ ያለው ፈተና/ሙከራ እንዲወስዱ ይፈቀድላቸዋል፡፡ | በዚህ ደረጃ በካውንስለር ወይም አስተዳዳሪወች ምንም አይነት ጣልቃ መግባት አይኖርም፡፡ |
| ደረጃ  2 | **ሆንብሎ ወይም አቅዶ ያልተገባን ስራ መስራት**<br>በተመሳሳይ የትምህርት ዘመን ተማሪው በአንድ የትምህርት ዘርፍ ወይም በሌሎች የትምህርት ዘርፎች የጥፋት መዝገብ ካለበት **ወይም** ያልተገባ ስራው ታቅዶ ወይም ታስቦበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡<br><br>*በዚህ ሂኔታ ፣ ተማሪዎች ከሌላ ተማሪ ሙሉ በሙሉ ኮርጀዋል፣ ወይም የራሳቸውን ያልሆነ ቃላትን ምንጩን ሳይጠቅሱ ተጠቅመዋል፡፡ ተማሪው/ዋ ከኢሌክትሮኒክ ምንጮችና ወይም ቁልፍ ቃላትንና ሀረግን በመቀየር ኮርጀው ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎች የኮረጁት የቤት ስራ ወይም ፈተና ከሆነ፣ ይህን ሆን ብለው እንዳደረጉት ይገመታል፡፡* | - ደረጃ  1 መልመጃዎችን፣ ፈተናዎችን፣ ሙከራዎችንና እንቆቅልሾችን ላይ  ማታለል  ሲፈጸም የሚተገበሩ ስርአቶች ወይም ደንቦች<br><br>እና<br>- የመማሪያክፍሉ መምህር የመልመጃዎች ቅጂ ና ሌሎች ከመልመጃው ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ለካውንስለሩ ያሳውቃል፡፡<br><br>እና<br>- ተማሪው/ዋ  እንዲያጠናቅቁ የመልመጃዎች ምርጫ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም የሚደረገው በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ የቀለም ትምህርት ስነምግባር ለማበረታታት ነው፡፡ | 1) ወላጅ ወይም አሳዳጊው ይጠራል፡፡<br>2) መምህሩ ቁሳቁሶችንና የድርጊቶችን አጭር መግለጫ በየክፍል ደረጃ ላሉ ካውንስለሮች ያስረክባል፡፡<br>3) ካውንስለሩ ተማሪውን/ዋን ለማማከር ያገኛቸዋል፡፡<br>4) የክፍል ደረጃው ረዳት ርዕሰ መምህርና መምህሩ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡ |
| ደረጃ  3 | **በተደጋጋሚ ያልተገባ ስራን መስራት**<br>በትምህርት አመታት ውስጥ አንድ ተማሪ በአንድ የትምህርት አይነት ወይም በሌሎች የትምህርት አይነቶች የጥፋት መዝገብ ከተገኘበት ነው፡፡<br><br>*ለዚህ የሚያደርሱ ነገሮች፣ የተሰረቀ የጹሁፍ ስራን ማስረከብ፣ ምንጮችን መፍጠር፣ ተመሳሳይ ስራን ከአንድ ጊዜ በላይ ማስረከብ፣ የተሰረቁ የፈተና ቁሳቁሶችን፣ ኢሌክትሮኒክስን አላአግባብ መጠቀም ወይም መልሶችን መጋራት ወይም ማተም፡፡* | - - ደረጃ  1 መልመጃዎችን፣ ፈተናዎችን፣ ሙከራዎችንና እንቆቅልሾችን ላይ  ማታለል  ሲፈጸም የሚተገበሩ ስርአቶች ወይም ደንቦች<br><br>እና<br><br>- የመማሪያክፍሉ መምህር የመልመጃዎች ቅጂ ና ሌሎች ከመልመጃው ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ለካውንስለሩ ያሳውቃል፡፡<br><br>እና<br><br>- ተማሪው/ዋ  እንዲያጠናቅቁ የመልመጃዎች ምርጫ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም የሚደረገው በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ የቀለም ትምህርት ስነምግባር ለማበረታታት ነው፡፡<br>AND<br><br>- ተማሪው/ዋ ለአንድ ቀን ከትምህርት ይታገዳል (ISS) ፡፡ | ከዚህ በላይ ከደረጃ  1-4 ያሉትን ይከተላል፡፡<br><br>እና<br><br>5) የድርጊቱ መግለጫ በተማሪው ሰነድ/ፋይል ላይ ይቀመጣል፡፡ |